# <u>የትግላችን ፍጥነት እንዳይቀንሰው !!</u>

*ከ1966ዓ/ም--- እስከ 1981 ዓ/ም ድረስ የትግራይ ሕዝብ ያካሄደው ትግል በዚያ ሂደት ላለፈ ካልሆነ ፤ከዚያ ውጪ ለሆነ ሁሉ እውነቱን ለመረዳት ይከብዳል። በዚያ ዘመን ለማመን የሚከብዱ የመስዋዕነት፣ የመተማመንና የክህደት ታሪኮች ኣልፈዋል። ዛሬ ኣንዳንድ የሕወሐት ተሐድሶ ፓርቲ ደጋፊዎችና ተጠቃሚዎች በመሆናቸው እውነቱን ቀይረው፣ እንደ ኣመቻቸው ጋግረው ሲያቀርቡት ይታያል። ሌሎቻችን ደግሞ የሕወሐት ተሐድሶ መሪዎች በሚፈጽሙት ድርጊትና እነሱ ከሚናገሩት ስለምንነሳ የተጨበጠ ግንዛቤ ለማግኘት ኣልተቻለም። ስለዚህ ዙሪያ ምላሽ የትግሉ ጉዞ እንዴት እንደነበረ ሳንገነዘብ ህዝቡንና የሕወሐት/ ኢህኣዴግ መንግስትን ባንድ ላይ መውቀጥ  ተደጋግሞ ይታያል። የትግራይ ህዝብ ከሕወሐት ድርጅት ጋር ሆኖ ያካሄደው ትግል፣ ልጆቹን ንብረቱን ያጣውና የከፈለው መስዋዕትነት ለብሄር እኩልነትና ኣንድነት፣ ለፍትህና ለዴሞክረሲ፣ ለሰላምና ኣብሮ ለመኖር ነበር። የመገንጠል ዓላማ የያዘ ፕሮፖጋንዳ አልነበረም። በዚያን ጊዜ የትግራይ ሕዝብ እንደ ህዝብ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው ነገር ኣልነበረም። ይሁን እንጂ ሕዝቡ ትግል በሚያካሄድበት ጊዜ ስውር የሆነ የመገንጠል ዓላማና ፀረ ኢትዮጵያ ስሜት ያላቸው መሪዎች የገመድ ጉተታ ያካሂዱ እንደነበረና በመጨረሻም ዴሞክራሲያዊ ሃይሉን በማዳከም ድርጅቱን ጠልፈው የጉዞውን ኣቅጣጫ የለወጡት መሆናቸው ይታወቃል ። ይህንን ብንናገር ለመቀበል የሚቸግራቸው ብዙዎች ናቸው። እውነቱ ላይ መግባባት ተገኝቶ ጠላትና ወዳጅ ተለይቶ መጓዝ ካልተቻለ የጉዟችንን ፍጥነት ይቀንሰዋል። ምክንያቱም የትግራይ ህዝብን የትግል ጉዞ በጥልቀት ካለመረዳት የተነሳ ቂጥራቸው ቀላል የማይባሉ የተዛቡ ኣስተያየቶች ህዝቡን ቅር የሚያሰኙና የአንድነት ትግሉን የሚጎዱ ፀያፍ ኣመለካከቶች ይሰነዘራሉ። እኛ በበኩላችን እነዚህ ኣስተያየቶች ምንጫቸው ህዝቡን ካለማወቅና የከሐዲው የሕወሐት ተሐድሶ ቡድን ተግባር በመመልከት መሰረት ያደረገ እንደሆነ እናውቃለን። በሌላም መልኩ ይህ ፀረ ጭቆና የመታገል ልምድ ያለው ህዝብ ዳግም እንዳይነሳና ተበታትኖ እንዲቀር የሚፈልጉ ኣይኖሩም ማለትም ኣይቻልም፣ ኣሉም። እነሱም ኣቶ መለስ ዜናዊ፣ ኣቶ ስብሐት ነጋ፣ ኣቶ ቴድሮስ ሐጎስና ወዘተ ናቸው። ኣቶ መለስ " የትግራይ ሕዝብ ታሪክ የሚሰራ ከሆነ በሕወሐት ስር መሆን ኣለበት " ሲሉ ተደምጠዋል። ኣቶ ቴድሮሰ ሐጎስ የትግራይ ሕዝብ ከሕወሐት ድርጅት ውጪ ሌላ ድርጅት ኣያስፈልገውም ብለዋል። ኣቶ ስብሓት" ሕገ መንግሰታችን" ካልተከበረ እንሄዳለን(እንገነጠላለን) ሲሉ ኣስጠንቅቀዋል ። ስለዚህ ይህንን ፍላጎታቸው ለመተግበር  የትግራይ  ሕዝብ እነሱ እና ተከታዮቻቸው በሚቆጣጠሩት የሕወሐት ድርጅት ስር መዋል ኣለበት እያሉን ነው ። ህዝባችን ከሕወሐት ውጪ የራሱ የሆነ ታሪክ መስራት ኣይፈቀድለትም ወይም ኣይችልም ማለት ነው። ስለዚህ ይህ ሕዝብ እንዲዳከምና እርስ በራሱ እንዳይተማመን፣ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋርም እንዲጣላ ማድረግ የሕወሐት ተሐድሶ ቡድን ዋነኛ ተግባር መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህ ውጭም ይህ ሕዝብ ተደራጅቶ ሃይል ሆኖ እንዳይነሳ የሚሰጉ ሌሎች ሃይሎችም ኣይኖሩም ማለት ደግሞ ኣይቻልም።*

*የሆነ ሁኖ በኛ በኩል መፍትሄው ህዝባችንን ከዚህ ኣፈና ነፃ ማውጣትና አውነተኛ ታሪካችንን ማስረዳት ብቻ መሆኑን ስለምንረዳ ተደራጅተን ስንታገል ቆይተናል ። ኣሁንም እየታገልን ነው። የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) በሚል ከ1995ዓ/ም እንደ ኣውሮፓውያን ኣቆጣጠር ጀምሮ  ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሃይል ኢትዮጵያዊያን በመተባበር የትግራይ ሕዝብን ሁኔታ እያስረዳ የሕወሐት ኢሕኣዴግ ማንነትንም እያጋለጠ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን ለሃገሩ የሚያስብ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። የትግራይ ዴሞክራሲየዊ ትብብር  (ት.ዴ.ት.) ከፓሪስ ኣንድ ጀምሮ ከዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ጋር እየተባበረ ሲታገል መቆየቱ እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች*

ሕብረት ከመመስረቱ በፊት በድርጅት ሕብረት ብቻ ኣመርቂ ስራ ለመስራት ያስቸግራል ፣ ከዚያ በላይ የሆነ የትግል ዘዴ መፍጠር ኣለብን የሚል ሐሳብ በማቅረብ ሲንቀሳቀስ ነበር ። ለማስታወስ ያህልም “ ሁላችን ፓለቲካዊ እንቅስቃሴያችንን፣ኢኮኖሚያዊ ሃይላችንን ፣ወታደራዊ ኣቅማችንን፣ በኣንድ ኣመራር ኣሰባስበን በጥምረት ወይንም ውሕደት ፈጥረን መታገል ኣለብን” የሚል ነበር። ሆኖም ግን ይህንን ሐሳብ ሲያቀርብ በወቅቱ ሐሳቡን የተቀበሉት ድርጅቶች ቁጥር ኣነስተኛ ነበሩ። ለዚህም ያቀርቧቸው የነበሩ የተቃውሞ ሐሳቦች ይህ ዓይነቱ የትግል ስልት ድርጅትን ያከስማል.. ወዘተ ) የሚል ፍራቻ ያዘለ ነበር ። ኣሁንም ይህንን ሐሳብ ይዘው የሚጓዙ ኣይጠፉም ። ውሎ ኣድሮ ግን ከተሞክሮና ከሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ባሁኑ ሰዓት ያ ሐሳብ ተቀባይነቱ እየጎላ መጥቶ ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት ድርጅቶች ቁጥራቸው የማይናቅ ነው። በማጠቃለል የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) ለኢትዮጵያ ኣንድነት እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ ሂደት መማፋጠንና እውን መሆን ጠቃሚ የትግል ስልቶችን በማቅረብ ግዴታውን እየተወጣ መሆኑ ኣይካድም ።

የትግራይ ዴሞክራሲዊ ትብብር(TAND) ዓላማውን ካልተረዱ ኢትዮጵያዊያን በኩል ከሚደርስበት ችግር፡በተጨማሪ የሕወሐት/ኢሕኣዴግ መንግስት ይህንን ድርጅት ከትግራይ ሕዝብ ለመነጠልና ድጋፍ እንዳያገኝ ለማድረግ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም።ይኸውም የእያንዳንዱ ድርጅት ኣባል ስም በማጥፋት፣ በማስፈራራትና እስከ ኣደጋ ማድረስ የደረሰበት ጊዜም ነበር። ኣሁንም ድርጅቱን ድራሹን ለማጥፋት ያለውን ሃይል በመጠቀም ላይ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው ። የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ደግሞ ት.ዴ.ት የኣማራ ትምክህተኛ መሳሪያ ነው፣ የትግራይ ሕዝብን ኣይወክልም፣የውጪ ጠላቶች መሳሪያ ነው፣ የትኛውም የትግራይ ተወላጅ ማንንም የተቃዋሚ ሃይል ቢደግፍ መሬትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ኣይሰጠውም... ወዘተ በማለት ቢያወናብድም የሕዝብን ጆሮና ኣመኔታ ሊያገኝ ኣልቻለም።

የሕወሐት/ኢሕኣዴግ የገዢ ፓርቲ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚያደርሰው ጭቆና መልኩ ብዙ ዓይነት ነው። በስልጣን ላይ ያሉት የሕወሐት ተሐድሶ መሪዎች በቤተሰብና ጋብቻዊ ዝምድና፣በአብሮ ኣደግነትና የትምህርት ጓደኝነት የተሳሰሩ ናቸው። ስልጣኑንም በተዋረድ ተከፋፍለውት ይገኛሉ። ሚስቲቱ በስልጣንዋ ተማምና ከበደለችህ የምትሄደው ወደ ባልዋ ነው። ወገንነቱ ጭቆናው ኣድልዎው ኣጎት፣ ኣክስት፣ ኣብሮ ኣደግ ወዘተ እያለ ይቀጥላል። የትግራይ ሕዝብ ኣማራጭ በሌለው የአፈና ቀለበት ውስጥ ተከቦ በመሰቃየት ላይ ነው።ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደዚሁ።የዚህ በደል ገፈት ቀማሽ የሆነው ግብር ከፍሎ ባስተማረ፣ ባሳደገና የሚወዳቸው ልጆቹን መስዋዕት እንዲከፍሉ ሸኝቶ ባታገለው ሕዘብ ላይ ነው። የህፃንነት ዕድሚያቸው ባሳለፉበት መሬትና ታግለንለታል በሚሉት ሕዝብ ላይ ነው ፣መሬቱ የኛ ኣይደለም ተብሎ ኢትዮጵያዊያን ኣይደለንም ለሚሉት ኣሳልፈው የሰጡት።የትግራይ ልጆች ከኤርትራዊያን ጋር ኣብረን ተባብረን ፋሽሽት ደርግን ካስወገድን በሗላ ኣብረን ሰላም ፈጥረን እንኖራለን በሚል ተስፋ ደማችን እንዲፈስ ካደረጉ በሗላ ለመታረቅ በማያመች ሁኔታ ኤርትራን በማስገንጠል ድብቅ ሕልማቸውን ዕውን ኣድርገዋል። ኣገራችን ኢትዮጵያ የባህር በር ኣልባ ሁና እንድትቀር ኣድርገዋል። ኣሁንም ኤርትራ ተገንጥላ እንድትቀር እስከ መጨረሻው ድረስ እየታገሉ ነው። የነዚህ ጉድ በዚህ ፅሑፍ ብቻ ተነግሮ ተጽፎም ኣያልቅም።

ይህ ከተከታዮቹ በስተቀር ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነጥሎ ብቻውን የቆመው ጨካኝ ከሐዲ ቡድን ከሕዝባችን በወረረው ንብረትና ወታደራዊ ሃይሉ ይሁን በሚያሰማራቸው ከሓዲ ሰላዮች እየተደገፈ ሊያጠቃንና ሊለያየን፣ ታሪክ ኣልባ ኣድርጎ ሊያስቀረን ብሎም ስልጣኑን ለማራዘም በየትኛውም መልኩ እየታገለን ይገኛል። በዚህም መሰረት የትግራይ ሕዝብ ይህንን ኣምባገነንና በትግርኛ ተናጋሪዎች ስም የሚነግድና የሚመፃደቅ ከሐዲ ቡድንን ለማንበርከክ ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ መልኩ በርትተን መታገል ይጠበቅብናል ብቻም ሳይሆን

የግድ ይለናል። ይህንን ሁኔታ ጀሮ ዳባ ልበስ ብለን ለማለፍ ብንሞክር ግን ከታሪክ ተወቃሽነትና ተጠያቂነት ልናመልጥ እንደማንችል በውል ልንረዳ ይገባናል።

የሕወሐት ኢሕኣዴግን ኣምባገነን መንግስት በሚያደርገው ፕሮፓጋንዳና በሚሰጠው ጊዚያዊ ጥቅም ምክንያት ከመታገልና ኣስተያየት ከመስጠት ተቆጥበው በሩቅ ሁኖ መመልከትን የመረጡ፤ በዝምድናና በጥቅም ተይዘው ኣፋቸው የተሸበቡ እንዳሉም እየተገነዘብን ነው። እነ ኣቶ ስብሐትና ኣቶ መለስ ኣሁን እንደሚሉት ሳይሆን ትናትና ለዴሞክራሲ፤ ለብሄር እኩልነት ለፍትህ መስፈን ከኛ ጋር በትግል ተሰልፈው እኛን መሪዎችን ኣምነው ግቡ ባልናቸው የጦርነት እሳት ገብተው የተለበለቡትና ህይወታቸውን የሰውት ደማቸው ሳይደርቅ እንዴት የጄነራል ማእርግ ኒሻን ስለተሰጠን ብቻ እንረሳቸው ኣለን ? ይህ ፀረ ዴሞክራሲና ከሐዲ ቡድን በኣመራር ደረጃ የነበራችሁትን በስውር ተደራጅቶ ሲበታትናቹህ ጓደኞቻችሁን እንደ ኣልባሌ ዕቃ ሲጥላቸው፤ በጠራራ ፀሐይ ከሜዳ እንደከብት ታጉረው ለዓመታት ሲታሰሩ ስለእውነት ስለፍትህ ለመናገር እንዴት ኣፋችሁን መክፈት ኣቃታችሁ ? እናቴ መሞታቸውን ያወቅኩት ዝም ሲሉ ነው እንደተባለው ሆነና ፤ ኣየናችሁ ታዘብናችሁ ኣይደል? በተለይ ኣንዳንዶቻችሁ ስም ሳንጠቅስ በታወቁት ዩኒቨርሲቲዎች ገብታችሁ ስትማሩ ገንዘብ ለመሰብሰብ፤ ለመክበርና ኣፋችሁን ለመዝጋት ኣይመስለንም ነበር ። ተው ኣይሆንም እናስተውል ! ። የኋላ ኋላ ምክንያት ለማቅረብ ብትሞክሩ ሰሚ የምታገኙ ኣይመሰለንም ። ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ይሆንባችኋልና ኣስቡበት ። ጊዜ ደግሞ ቆሞ ኣይጠብቅም በየቀኑ የተሰራውን እየመዘገበ ይጓዛል ። ጀግና ማለት ደግሞ ለሰው ልጅ መብትና ለሕግ የበላይነት መቆም ብቻ ነው እስካልተባለ ድረስ እናንተ እኮ ትናትና ድፍረትና ጀግንነታዊ ኣመራር የሰጣችሁ ሰዎች እንደነበራችሁ እናውቃለን።እና ተው ከሰፊው ሕዝብ ጋር ቁሙ። እነዚያ በዓይናችሁ እያያችሁ ደማቸው የፈሰሰውና ኣካላቸው የጎደለውን ታጋዮችን ኣስታውሱ። ያ ትግል ኣካሂዶ ራቁቱን የቀረው ድሉን የተቀማው፤የትግራይ ሕዝብን ኣስቡትና ከኛ ጋር ወደ ህዝባዊ ትግሉ ተቀላቀሉ ። ለፍትህ ለዴሞክራሲና ለሕግ የበላይነት ታገሉ ። የምታውቁትን ኣካፍሉ የአቅማችሁን ኣስተዋፅኦ ከማድረግ ኣትቆጠቡ። ያለውን የወረወረ ፈሪ ኣይባልም እንደተባለው ለማለት እንወዳለን።

በውጭ ተሰድዶ ያለው የትግራይ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ በትግሉ ላይ እየተሳተፈ ነው ባይባልም በመጠኑ ባለው ኣቅም እየታገለ ነው። እሰካሁን ድረስ ት.ዴ.ት. እና በቅርቡ የተመሰረተው “ ዓረና “ ተጨምሮ ሁለት የፖለቲካ ድርጅትና በተለያዩ የሲቪክ ማሕበራት ውስጥ ተደራጅቷል።እነዚህ እንቅስቃሴዎች ለሕግ የበላይነት እየታገሉ እንደሆነ የታወቀ ነው። በሃገሩ ውስጥ ሆኖ ፍዳውን ከሚያየው ሕዝብም የጠነከረ ትስስር ኣላቸው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ተጠቃለው ኣንድ ሃይል ሁነው መውጣታቸው የማይቀር ነው። ሆኖም ግን ተባብረው ሊሰሩ ቢችሉ ኣመርቂ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ የታወቀ ነው።በመሆኑም ይህንን ዕውን ለማድረግ የየበኩላቸውን ኣስተዋፅኦና ጥረት ቢያደርጉ መልካም ነው ።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር/ ት.ዴ.ት. የሕወሐት/ኢሕኣዴግን ኣምባገነን መንግስት ፕሮፖጋንዳ እየታገለ ሕዝብን ለትግል እያነሳሳ መሆኑም ግልጽ ነው። የትግራይ ሕዝብ በቋንቋውና በሚፈልገው ዓይነት ኣደረጃጀት በማሰማራት ጠላቶቹ እና ወዳጆቹን ለይቶ ማወቅ እንዲችል እየጣረ ነው። ድርጅታችን በቅድሚያ ጠባብነት ትምክህትንና ጥላቻን ለማጥፋት የሚታገለው፤ኢትዮጵያ ኣገራችን ኣንድነትዋ መብትዋ ተከብሮ የሕግ የበላይነትና እኩልነት የነገሰባት ኣገር እንድትኖረን ነው።

በስልጣን ላይ ያለው የገዢ ፓርቲ በተቃዋሚ ወገን የተሰለፉትን ሃይሎችና በዚያ የትግል ዘመን የጎላ ሚና የተጫወቱትን ግለሰቦች ለምሳሌ እንደ ኣቶ ኣረጋዊ በርሄ ዓይነቱን ድርጅታችን የከዳ ነው፤ከትምክህተኛ ኣማራ ጋር በማበር ይንቀሳቀሳል በማለት ሲወነጅል፤ ኣቶ

*ገብሩ ኣስራትንም ከቅንጅት ጋር በመተባበር ትግራይን ለማስመታት እየጣረ ነው፣ ገብሩ ኣስራት ኣማራ ነው..ወዘተ በማለት፣ ኣቶ ስየ ኣብርሃንም በሙስና የተጨማለቀ ነው.. ወዘተ በማለት የውሸት ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨት የተቃዋሚ ሃይላችንን እንቅስቃሴያችንን ለማዳከም ያለ የሌለውን ሃይል ኣሰማርቶ ሲታገለን ይታያል ።*

*የሕወሐት/ኢሕኣዴግ ገዢ ፓርቲ የተቃዋሚ ሃይሉን ውሰን ድክመትንም እየመዘዘ ለራሱ ኣመቺነት ሲጠቀምበት ሃይላችንን ለመበታተን ሲሞክር ስንመለከት በጣም እናዝናለን ። የስርዓቱ ተቃዋሚ ነን ከምንል ኢትዮጵያዊያን የሲቪክ ማሕበራትና የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ግለሰቦችም ጭምር ሕዝብንና መንግስትን ሳይለዩ በኣንዳንድ በኢሕኣዴግ ኣምባገነን መንግስት ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ሊያደርሱ በሚችሉ የታወቁ የትግራይ ተወላጆች ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲካሄድባቸው ማየት በጣም ከማሳዘኑም ሌላ ለኢሕኣዴግ ዱላ እንደማቀበል ሆኖ ይቆጠራል የሚል እምነት ኣለን ። ለምሳሌ፣ ትግሬዎች ማመን ኣይቻልም፣ ሁሉም የኢሕኣዴግ ደጋፊ ናቸው። ኣቶ አረጋዊ በርሄ ትግራይን ለማስገንጠል ሲታገል የነበረ ነው። ኣቶ ገብሩ ኣስራት ከኢሕኣዴግ ጋር ሆኖ ሲጨፈጭፈን የነበረ ሰው ነው ። ሰየ ማን ነው የኢትዮጵያ ጀግና ያደረገው ? በማለት ማብጠልጠልና ጥላቻን መንዛት ፣ ሌላው ደግሞ በእነ ዶ/ር ታየ ወልደሰማያት፣ኢንጅነር ሃይሉ ሻወል፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወዘተ ላይ የሚነዛው ኣሉቧልታና ማጥላላት ተልእኮው ምን እንደሆነ ሊገባን ኣልቻለም ። እባካችሁን በቁስል ላይ እሾህ እንደሚባለው በተበደለ ዜጋ እና ሕዝብ ላይ ጥላቻ መንዛት እናቁም ። የስርዓቱ ተቃዋሚዎች ሁነን ለምን የኢሕኣዴግ ስራን እንደምንሰራ ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው ። ጠላትና ወዳጅን ለይተን በጠላታችን ላይ ክንዳችን ማስተባበር ኣለብን። ሰልፋችን ከማን ጋር ነው ? መታወቅ ኣለበት ። ይህ ካልሆነ ግን መራመድ ኣይቻልም። የትግል ጉዟችንን ፍጥነት እንዳይቀንሰው ያሰጋል። ስለዚህ በጉዳዩ እንድናስብበት ኣደራ እላለሁ ።*

*( እነዚህ ስማቸው ከላይ የጠቀስኳቸው ግለሰቦች ስሕተት ፈጽመው ከሆነም በስነሰርዓት በውይይት መታረም የለባቸውም ማለቴ እንዳልሆነ ግን ይታወቅልኝ ።)*

*የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ኣባል*

*መኮነን ዘለለው*

*ኖቬምበር 10፣ 2007*

*ኣስተያየት በዚህ ኣድራሻ እቀበላለሁ*
email፡ mokonnenz@hotmail.com